# ለካ አላት

የባርነት ዘመኗ - ስቃይዋ ያለቅጥ ረዝሞ
የሰቆቃ ለቅሶዋ - ከትውልድ ትውልድ ከርሞ
የጥላቻ ባህሩን - በፍቅር በትር  ከፋይ
ዘጸአቷን ፈጻሚ - ከንዓኗን የሚያሳይ
እምባዋን ከጉንጯ 'ሚያብስ - ልጆቿን የሚያሳማማ
ፈጣሪ የላትም ስንል - ኤሎሄዋን 'ሚሰማ

ከእባብ እንቁላል እርግብ -   ከተኩላ ሆድ በግ ሰርቶ
ለፈ'ሮን ቀንበር ፍዳ - ሁሌ የማይተዋት ትቶ
ታምራቱን የሚያሳይ - ዛሬም የሚታደጋት
ኢትዮጵያ ለካ አምላክ አላት!

ጴጥሮስ ደጀኔ

ቶሮንቶ፤ካናዳ